04

7ኛ ዓመት ቁጥር 7
7th Year No. 7

ባህር ዳር መጋቢት 21 ቀን 1994 ዓ.ም
Bahir Dar March 30,2002

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

ዝክረ ሕግ

ZIKRE HIG

Of the Council of the Amhara National Regional State in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ	Issued under the auspice of the Council of the Amhara National Regional State	☒ 1324 ያንዱ ዋጋ ብር 3.30 Unit price

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 63/1994 ዓ/ም

የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት ህግ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት፣ የኮሚቴዎች አደረጃጀትና አሠራር መወሰኛ አዋጅ

Contents

Proclamation No. 63/2002

Proclamation for Defining the Legislative procedure, Committee Organization and Operation of the Amhara National Regional Council.

አዋጅ ቁጥር 63/1994 ዓ.ም
በአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት የህግ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት፣ የኮሚቴዎች አደረጃጀትና አሠራርን ለመወሰን የወጣ አዋጅ

ጥቅምት 26 ቀን 1994 ዓ.ም ተሻሽሎ የወጣው የአማራ ብሔራዊ ክልል ሀገመንግሥት በአንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የብሔራዊ ክልሉ ምክር ቤት የክልሉ ህግ አውጪ አካል እንደሆነ የሚደነግግ በመሆኑ፣

ይህንኑ ህግ የማውጣት ሥልጣኑን መሠረት አድርጉ የክልሉ ምክር ቤት በህገመንግሥቱ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት እንዲሁም በሕዝቡ የተጣለበትን ኃላፊነት በበለጠ ለመወጣት ይቻለው ዘንድ ከህገመንግሥቱ ጋር የተገናዘበና ብቃት ያለው ውስጣዊ አደረጃጀት፣ የተሟላ የአሠራር ስልትና ዝርዝር ሥነ-ሥርዓቶች መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት ተሻሽሎ በወጣው የክልሉ ህገመንግሥት አንቀጽ 49/3/1 በተሠጠው ሥልጣን መሠረት የሚከተለውን አውጇል::

ክፍል አንድ
ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ " የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት ህግ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት፣ የኮሚቴዎች አደረጃጀትና የአሠራር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 63/1994ዓ.ም " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

Proclamation No.63/2002
Proclamation for Defining the Legislative Procedure, Committee Organization and Operation of the Amhara National Regional Council

WHEREAS, it is provided in Article 49 sub-article 1 of the November 5,2001 Revised Constitution of Amhara National Region that the National Regional Council is the Legislative body of the Region;

WHEREAS, pursuant to this power of legislation it has become necessary to lay down efficient internal organization competent modus operandi and rules of procedure in line with the Constitution which enables the Regional Council to discharge its powers and duties enshrined in the Constitution and the responsibilities entrusted to it by the public as well;

NOW, THEREFORE, The council of the Amhara National region, in accordance with the powers vested in it under Article 49/3/1 of the revised constitution of the region, hereby proclaims as follows:

PART ONE
General

1. Short Title

This Proclamation may be cited as " The Proclamation for Defining the Legislative Procedure, Committee Organization and Operation of the Amhara National Regional Council No. 63/2002".

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. " ምክር ቤት " ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት ነው፤
2. " ቋሚ ኮሚቴ " ማለት በህግ ተወስኖ በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር ዙሪያ በቋሚነት የሚሠራ ሆኖ በህገ-መንግሥቱ አንቀጽ 49/ንዑስ አንቀጽ 3/4 መሠረት ምክር ቤቱ የሚያቋቁመው ቋሚ ኮሚቴ ነው፤
3. " የጋራ ኮሚቴ " ማለት አንድ ጉዳይ በምክር ቤቱ ወይም በአፈ-ጉባኤው አማካኝነት ከአንድ በላይ በሆኑ ቋሚ ኮሚቴዎች እንዲታይ ሲመራ ጉዳዩን በአንድነት የሚያጠኑ ወይም የሚያከናውኑ ኮሚቴዎች ናቸው፤
4. " አፈ ጉባዔ " ወይም " ምክትል አፈ-ጉባዔ " ማለት እንደ ቅደም ተከተላቸው የምክር ቤቱ አፈ-ጉባዔ ወይም ምክትል አፈ-ጉባዔ ነው፤
5. "የመጀመሪያ ንባብ" ማለት የህግ ረቂቅ የማቅረብ መብት ያላቸው አካላት በአጀንዳነት እንዲያዝላቸው ለአፈጉባኤው የሚያቀርቡበትና ረቂቅ ህጉ ለበለጠ እይታ ለሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ ከመመራቱ በፊት በአፈጉባኤው አማካኝነት በዝርዝር የሚታይበት ሁኔታ ነው::
6. " ሁለተኛ ንባብ " ማለት ከመጀመሪያው ንባብ በኋላ ለበለጠ እይታ ወደሚመለከታቸው ቋሚ ኮሚቴ ተመርቶ ቋሚ ኮሚቴው ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በሚያደርገው ውይይት ያጠናቀረው የውሣኔ ሃሳብና አስተያየት ለምክር ቤቱ አባላት ቀርቦ የሚደረገው የውይይት ሁኔታ ነው፤
7. " ሦስተኛ ንባብ " ማለት ከሁለተኛ ንባብ በኋላ ምክር ቤቱ በበለጠና በሰፋት እንደገና እንዲታይ ለሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ የመራው ረቂቅ ህግ እንደገና ወደ ምክር ቤቱ ተመልሶ የሚደረገው የውይይት ሁኔታ ነው፤
8. " ህገ መንግሥት " ማለት ጥቅምት 26 ቀን 1994 ዓ.ም ተሻሽሎ የወጣው የአማራ ብሔራዊ ክልል ህገ-መንግሥት ነው::

ክፍል ሁለት

የምክር ቤቱ ዋና ዋና ተግባራትና የአሠራር ሥርዓት

3. የምክር ቤቱ አጠቃላይ ተግባራት

ምክር ቤቱ በህገ መንግሥቱ አንቀጽ 49 ከተሠጠው ባለብዙ ፈርጅ ሥልጣን የሚመነጩ ሆነው የሚከተሉት አጠቃላይ ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

2. Definition

Unless the context otherwise requires, in this proclamation:

1. " Council" means the Amhara National Regional Council;
2. " Standing Committee" means the Standing Committee formed pursuant to Article 49 sub-articles 3/4 of the Constitution to act perpetually within its legally provided jurisdiction;
3. "Joint Committee" means more than one Standing Committees that collectively study a case referred to them by the Council or the Speaker;
4. "Speaker" or "Deputy Speaker" means the Speaker and Deputy Speaker, respectively, of the Council;
5. "Preliminary Reading" means the presentation of a draft legislation by authorized bodies to the Speaker for consideration as an agenda item and which the Speaker thoroughly examines before referring to the concerned Standing Committee.
6. "Second Reading" means the discussion of the Council members resolutions and opinion of concerned bodies gathered by the Standing Committee to which the draft legislation was referred for further inspection subsequent to the Preliminary Reading.
7. "Third Reading" means the discussion of Council members on the returned draft legislation, which was earlier referred to the concerned Standing Committee for further re-examination subsequent to the Second Reading.
8. "Constitution" means the Revised Constitution of the Amhara National Region issued on November 5,2001.

PART TWO

Major Duties and working Procedure of the Council

3. Major Duties of the Council

The Council, deriving its multiple powers from Article 49 of the Constitution, shall have the following major duties and responsibilities:

1. ህጐችንና ደንቦችን የማውጣት፤
2. የክልሉን መንግሥታዊ አካላት አሠራር የመመርመርና የመከታተል፤
3. ቋሚ ኮሚቴዎችንና ሌሎች ልዩ ልዩ ኮሚቴዎችን ማቋቋም፣ ሪፖርቶቻቸውን የማዳመጥ፣ ውሣኔዎችንና መመሪያዎችን የመስጠት።

ንዑስ ክፍል አንድ

የህግ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት

4. የህግ ረቂቅ የማመንጨት መብት ስላላቸው አካላት

1. ህግን በማመንጨት ረቂቅ የህግ ሠነድ ለምክር ቤቱ የሚያቀርቡት አካላት ከዚህ በታች የተመለከቱት ናቸው።
   - ሀ. አስፈፃሚ አካላት
   - ለ. የዳኝነት አካላት
   - ሐ. የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች
   - መ. የምክር ቤቱ አባላት
   - ሠ. ተጠሪነታቸው ለምክር ቤቱ የሆኑ ሌሎች መንግሥታዊያን አካላት
   - ረ. አፈ-ጉባዔው
   - ሰ. በተዋረድ የሚገኙ ምክር ቤቶች
   - ሸ. የተደራጁ የህብረተሠብ ክፍሎች
2. ከላይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1/መ/ በተገለፀው መሠረት የሚቀርብ ማናቸውም የህግ ረቂቅ በጽሁፍ ሆኖ ቢያንስ የምክር ቤቱን ስምንት አባላት የድጋፍ ፊርማ ማግኘት አለበት።
3. ማናቸውም የህግ ረቂቅ በአፈ-ጉባዔው በኩል ለምክር ቤቱ ይቀርባል።

5. ስለመጀመሪያ ንባብ

1. አፈጉባኤው በቀረበለት አጀንዳ ላይ የመጀመሪያ ንባብ ያካሂዳል፤
2. የህግ ረቂቁ የመጀመሪያ ንባብ እንዳበቃ አፈጉባኤው ለሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ ለበለጠ አይታና ጥናት ይመራዋል፤
3. ረቂቅ ህጉ የተመራለት ቋሚ ኮሚቴ ጉዳዩን አጥንቶ የውሳኔ ሐሳቡን ለምክር ቤቱ ለማቅረብ ቢያንስ የአስራ አምስት /15/ የስራ ቀናት ማግኘት ይገባዋል።

1. Enacting laws and regulations;
2. Examining and monitoring the operations of governmental bodies of the Region;
3. Establishing Standing Committees and various other committees, hearing their reports, and passing decisions and directives.

Sub-Section One

Legislative Procedure

4. Bodies Having the Right to Initiate Drafts Legislations

1. Bodies that may initiate a legislation and submit its draft to the Council are the following:
   - a. Executive bodies
   - b. Judicial bodies
   - c. The Standing Committees of the Council
   - d. Council members
   - e. Other Governmental bodies which are accountable to the Council
   - f. The speaker
   - g. Hierarchical Councils
   - h. Organized sections of the society.
2. A draft legislation submitted under sub-article 1(d) of this Article shall be made in writing and endorsed by the signatures of at least eight members of the Council.
3. All draft legislation shall be submitted to the Council through the Speaker.

5. Preliminary Reading

1. The Speaker shall conduct preliminary Reading of the agenda presented to him.
2. Subsequent to the preliminary Reading the Speaker shall refer it to the concerned Standing Committee for further consideration and study.
3. The Standing Committee to which the case is referred shall have at least fifteen (15) days to study the draft legislation and submit its proposals to the Council.

6. ሁለተኛ ንባብ

1. የመጀመሪያው ንባብ ከተጠናቀቀ በኋላ አፈ-ጉባዔው ለሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ በተመራው የህግ ረቂቅ ላይ የተጠናቀረውን የውሣኔ ሃሳብና አስተያየት በቋሚ ኮሚቴው አማካኝነት ለምክር ቤቱ እንዲነበብ ያደርጋል፤

2. አፈ-ጉባዔው በቀረበው የውሣኔ ሃሳብ ላይ ዝርዝር ውይይት እንዲደረግ መድረክ ይከፍታል፤

3. በዚህ ውይይት የህግ ረቂቁ ሊጠቃለል ካልቻለ ለጸማም እይታ ወደሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ ተመልሶ ሊመራ ይችላል። ውይይቱ በበቂ ሁኔታ ከተጠናቀቀ ግን ህግ ሆኖ እንዲወጣ ይወሰናል።

7. ሦስተኛ ንባብ

1. ረቂቅ የህግ ሠነዱ ዳግም የተመራለት ቋሚ ኮሚቴ የሚያሻሽለውን አሻሽሎ የመጨረሻ የውሣኔ ሃሳቡን ለምክር ቤቱ በንባብ እንዲያሰማ ይደረጋል፤

2. በቀረበው የመጨረሻ የውሣኔ ሃሳብ ላይ ምክር ቤቱ በቂ ውይይት በማካሄድ ህግ ሆኖ እንዲወጣ ሊወስን ይችላል።

8. ሕጉ በስራ ላይ ስለሚውልበት ሁኔታ

1. አፈ-ጉባዔው የህግ ረቂቁን ምክር ቤቱ መክሮ የተስማማበትና ያፀደቀው መሆኑን በመግለጽ የብሔራዊ ክልሉ ፕሬዚዳንት ይፈርምበት ዘንድ ይልከዋል፤

2. ሠነዱ ለብሔራዊ ክልሉ ፕሬዝዳንት በደረሰ በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ ካልተፈረመ ህግ ሆኖ ይወጣል።

3. የፀደቀው ህግ በአፈ-ጉባዔው አማካኝነት ቁጥር ተሰጥቶት በክልሉ ዝክረ ሕግ ጋዜጣ ይታተማል።

ንዑስ ክፍል ሁለት

የመንግሥታዊ አካላትን አሠራር ስለመመርመርና ስለመከታተል

9. ሪፖርት ስለማቅረብ

1. እያንዳንዱ የክልሉ መንግሥት አካል በአፈ-ጉባኤው ወይም በሚመለከተው የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ አማካኝነት ጥሪ ተደርጉለት በተመደበለት የጊዜ ሠሌዳ መሠረት ለምክር ቤቱ ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ አለበት፤

2. በሌላ ሰው እንዲቀርብ አስገዳጅ ሁኔታ ካላጋጠመ በስተቀር ሪፖርቱ በመስሪያ ቤቱ ኃላፊ ይቀርባል፤

6. Second Reading

1. Subsequent to completion of Preliminary Reading, the Speaker shall cause the draft proposals and comments compiled by the pertinent Standing Committee to be read out to the Council by the Standing Committee.

2. The Speaker shall open a forum for elaborate discussions on the submitted legislation draft proposals.

3. Where it may not be possible to conclude the draft legislation during this discussion it shall be again referred to the concerned Standing Committee for a second consideration; where the debate is found conclusive, it shall be decided that the draft is enacted as a law.

7. Third Reading

1. The Standing Committee to which the draft legislation is referred for further consideration and study shall be caused to read out its final recommendations to the Council.

2. Subsequent to holding sufficient deliberations on the draft proposals submitted, the council may decide that the draft be enacted as a law.

8. Enactment of the Law

1. The Speaker shall, together with a statement that the draft legislation has been considered and approved by the council, pass it to the President f the Region, for signature.

2. The legislation shall come in to force if the President fails to sign up on it with in fifteen /15/ days after its having been received by him.

3. The approved legislation shall be numbered by the Speaker and thereby published in the Regional Zikre Hig Gazette.

Sub-section Two

Monitoring and Examining Operation of Governmental Bodies

9. Submission of a Report

1. Any executive body of the Regional Government shall have the obligation to report to the Council within the set timetable when invited to do so by the Speaker or the concerned chairperson of a Standing Committee of the Council.

2. Unless circumstances compel that this be submitted by another person, the report shall be presented by the head of the Government Office.

3. ሪፖርቱ በኃላፊው ተወካይ ሊቀርብ የሚችለው ኃላፊው ሊቀርብ ያልቻለበትን ምክንያትና በተወካዩ አማካኝነት የሚቀርብ መሆኑን ለአፈ-ጉባዔው አስቀድሞ በማሳወቅ ይሆናል::

10. ስለ አስፈፃሚ አካላት አጠቃላይ ሪፖርት

የክልሉ መንግሥት አስፈፃሚ አካላት ሪፖርት በተጠቃለለ መልኩ ተዘጋጅቶ በርዕሰ መስተዳድሩ ይቀርባል ::

11. የቀረበውን ሪፖርት ስለመመርመርና ውሣኔ ስለመስጠት

1. የሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴና የምክር ቤቱ አባላት በአፈ-ጉባዔው በሚሰጣቸው ቅደም ተከተል መሠረት መንግሥታዊ አካላትን በተመለከተ የቀረበውን ሪፖርት ተንተርሰው ጥያቄዎችንና አስተያየቶችን ሊያቀርቡ ይችላሉ ::

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በተሰጡት መልሶች ዙሪያ ተጨማሪ ጥያቄዎችና አስተያየቶች እንዲቀርቡ ይደረጋል::

3. ሪፖርቱን አስመልክቶ የማጠቃለያ አስተያየት መስጫ መድረክ ሊከፈት ይችላል:: አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም ምክር ቤቱ የሚመለከተውን ቋሚ ኮሚቴ ተጨማሪ ማጣራትና ምርመራ አድርጐ ዝርዝር ሪፖርት እንዲያቀርብለት ሊያዝ ይችላል፤

4. ምክር ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የቀረበውን ሪፖርት አዳምጦ ተቀባይነት ያለውና የተሟላ ነው ብሎ ካመነ የሚያፀድቀው ሲሆን መሠረታዊ ችግር አለበት ብሎ ያመነ እንደሆነ ግን አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል::

12. የቋሚ ኮሚቴዎችንና ሌሎች ኮሚቴዎችን ሪፖርት ስለማዳመጥ

1. የምክር ቤቱ ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎች አፈ-ጉባዔው በሚያወጣው የጊዜ ሠሌዳ መሠረት በተሰጣቸው ተግባርና ኃላፊነት ዙሪያ በአመራሮቻቸው ወይም በተወካዮቻቸው አማካኝነት ለምክር ቤቱ የሥራ ሪፖርት ያቀርባሉ፤

2. ቋሚ ኮሚቴዎች የሚያቀርቡት የሥራ ሪፖርት በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ይሆናል:-

   ሀ. ዓመታዊና ጠቅላላ የሥራ አፈፃፀም

   ለ. በምክር ቤቱ አማካኝነት በየጊዜው የሚመሩላቸው ጉዳዮች፤

3. የጊዜያዊ ኮሚቴዎች ሪፖርት በተሠጣቸው የተለየ ተልዕኮ ላይ የተወሠነ ይሆናል፤

3. Where the report is presented by a representative of the official, the head of the office shall make an advance notification of this to the Speaker explaining the reasons for failing to show up personally.

10. Compiled Report of Executive Bodies

General report of the executive bodies of the Regional Government shall be presented by the Head of the Government.

11. Examining and passing Decisions on the submitted Reports.

1. The concerned Standing Committee and Council members shall, according to the order given to them by the Speaker, raise questions and forward suggestions or comments on the reports submitted about the various governmental bodies.

2. Additional questions and comments shall be presented on the explanations and answers given in accordance with sub-article 1 of this Article.

3. A forum may be created for making concluding statements about the reports; where necessary, the Council may order that a concerned Standing Committee make additional investigation and study and submit a detailed report.

4. The Council shall, subsequent to hearing the report specified in sub-article 3 of this Article, and finding it acceptable and convincing, approve it forthwith; where the Council belives that the report is with a basic problem, it shall take the necessary action.

12. Hearing Report of Standing Committees and Other Committees

1. The Standing and Ad-Hoc Committees of the Council shall, according to the timetable set by the Speaker, present performance reports concerning their duties and responsibilities through their leadership or their representatives.

2. The performance report presented by the Standing Committees shall focus on the following matters:

   a. Annual and general work performance

   b. Cases referred to them occasionally by the Council

3. The report of the Ad-Hoc Committees shall be restricted to the specific mission assigned to them.

4. የምክር ቤት አባላት በቀረበው ሪፖርት ዙሪያ ውይይት ያደርጋሉ፣ አስተያየት ይሰጣሉ፣ ውሣኔዎችን ያሳልፋሉ ::

ክፍል ሶስት

የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች አደረጃጀት፣ ኃላፊነትና አሠራር

13. የቋሚ ኮሚቴዎች አደረጃጀትና ተዋጽኦ

1. ምክር ቤቱ የሚከተሉት ቋሚ ኮሚቴዎች ይኖሩታል:-

   ሀ. የኢኮኖሚ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ

   ለ. የአቅም ግንባታና የማህበራዊ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣

   ሐ. የበጀትና የመንግስት ሂሣብ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣

   መ. የህግና አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና፣

   ሠ . የሴቶች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ::

2. እያንዳንዱ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢውንና ፀሐፊውን ጨምሮ ቁጥራቸው እንዳስፈላጊነቱ የሚወሰን ከምክር ቤቱ አባላት መካከል በቀጥታ የሚመረጡ አባላት ይኖሩታል::

3. አንድ የምክር ቤት አባል በአንድ ጊዜ ከአንድ ቋሚ ኮሚቴ በላይ አባል ሆኖ ሊመረጥና ሊሠራ አይችልም::

4. የቋሚ ኮሚቴዎች ሰብሳቢዎች ተጠሪነታቸው ለየሚመለከታቸው ኮሚቴና ለአፈ-ጉባዔው ይሆናል::

14. የቋሚ ኮሚቴዎች የወል ሥልጣንና ተግባር

የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች የሚከተሉት የወል ሥልጣንና ተግባራት ይኖራቸዋል::

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5, 6 ና 7 ድንጋጌዎች መሠረት በተመሩላቸው የህግ ረቂቆች ላይ የውሣኔ ሃሳቦችና አስተያየቶችን ለምክቤቱ የማቅረብ፣

2. በየቋሚ ኮሚቴዎች ሥር እንደየአግባቡ በተደለደሉት መንግሥታዊ አካላት አሠራር ላይ ምርመራና ክትትል የማድረግ፣

4. The Council members shall hold debate on the report presented to them, give comments and pass decisions.

PART THREE

Organization, Responsibilities and Operation of Standing Committees

13. Organization and Composition of Standing Committees

1. The Council shall have the following Standing Committees:

   a. Economic Affairs Standing Committee

   b. Capacity Building and Social Affairs Standing Committee

   c. Budgetary and Government Finance Affairs Standing Committee

   d. Legal and Administrative Affairs Standing committee and

   e. Women's Affairs Standing Committee.

2. Each Standing Committee including its Chairperson and Secretary shall have members, whose number may be determined as deemed necessary, directly elected from among Council members.

3. Any member of the Council shall not be elected as member and serve simultaneously in more than one Standing Committee.

4. The Chairpersons of the Standing Committees shall be accountable to the relevant Committee and to the Speaker.

14. Common Powers and Duties of Standing Committees

The Council's Standing Committees shall have the following common powers and duties:

1. Submit to the Council proposals and suggestions made on the various draft legislations referred to them in line with the Provisions specified in articles 5, 6 and 7 of this Proclamation.

2. Examine and follow up the operation and performance of governmental bodies assinged as deemed appropriate to each Standing Committee.

3. ከየኮሚቴዎቻቸው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጥናቶች የማካሄድና የክልሉ ፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎች ተግባራዊ መሆናቸውን የመከታተል፣

4. ልዩ ልዩ ዐውደ ጥናቶችንና የውይይት መድረኮችን የማዘጋጀትና የልምድ ልውውጦችን የማድረግ፣

5. ከአፈ-ጉባዔው የሚሰጧቸውን ሌሎች ተዛማች ተግባራት የማከናወን።

15. ስለ ኮሚቴ ሰብሳቢዎች ሥልጣንና ተግባር

የቋሚ ኮሚቴዎች ሰብሳቢዎች ከዚህ በታች የተመለከቱት የወል ሥልጣንና ተግባራት ይኖሯቸዋል።

1. ኮሚቴዎችን በመወከል ከልዩ ልዩ አካላትና ባለሥልጣናት ጋር የሥራ ግንኙነቶችን የማድረግ፣

2. የየኮሚቴዎቻቸውን ሥራ በበላይነት የመምራት፣ የማስተባበርና የስብሰባ ሥነ-ሥርዓቶቻቸውን የማስጠበቅ፣

3. ጥሪ የተደረገላቸው ተጋባዥ እንግዶች እንዲገኙ ቅድመ ሁኔታዎችን የማመቻቸት፣

4. ለምክር ቤቱ የሥራ ዘገባ የማቅረብና፣

5. ከአፈ ጉባዔውና ከምክር ቤቱ በተለይ የሚሰጧቸውን ሌሎች ተግባራት የማከናወን።

16. የኮሚቴ ፀሐፊዎች ሥልጣንና ተግባር

የቋሚ ኮሚቴ ፀሐፊዎች ከዚህ በታች በተመለከቱት የወል ሥልጣንና ተግባራት ይኖሯቸዋል፦

1. ሰብሳቢዎቹ በማይገኙበት ጊዜ ተክተው የመሥራት፣

2. የየኮሚቴዎቹ ሠነዶችና ቃለ-ጉባዔዎች በአግባቡ መያዛቸውንና መጠበቃቸውን የማረጋገጥ፣

3. በሰብሳቢዎቹ የሚሠጧቸውን ሌሎች ተግባራት የማከናወን።

17. የቋሚ ኮሚቴዎች አጠቃላይ አሠራር ስነ- ስርዓት

የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች የሚከተሉት ዋና ዋና ያሠራር ስልቶችና ሥነ-ሥርዓቶች ይኖሯቸዋል፦

1. ከመጀመሪያ ንባብ በኋላ በአፈ-ጉባዔው በኩል ለቋሚ ኮሚቴዎች የተመሩ ረቂቅ ሕጐችን እንደየሁኔታው፦

3. Follow up the implementation of the Region's policies as well as overseeing the launching of studies pertinent to each Committee.

4. Preparing various workshops and discussion and experience-sharing forums.

5. Cary out other related activities assigned to them by the Speaker.

15. Powers and Duties of Committee Chairpersons

The Chairpersons of Standing Committees shall have the following common powers and duties:

1. Make business contacts with various bodies and officials on behalf of Committees.

2. Direct and coordinate the work of the Committees, and keep order of conferences;

3. Facilitate conditions for the attendance of invited guests;

4. Present performance reports to the Council;

5. Undertake other activities specially assigned to them by the Speaker and the Council.

16. Powers and Duties of Committee Secretaries

The Secretaries of Standing Committees shall have the following common powers and duties:

1. Act in place of Chairpersons when these may not be available;

2. Ensure that committee documents and minutes are properly recorded and preserved;

3. Undertaking such other activities as assigned to them by the Chairpersons.

17. Working Procedure of Standing Committees

The Council's Standing Committees shall have the following main working methods and procedures:

1. Draft legislations referred to Standing Committees by the speaker subsequent to the preliminary Reading, as the case may be:

ሀ. ማስታወቂያ በማውጣት፣

ለ. አስረጅ አካላትን በመጋበዝ፣

ሐ. የሕዝብ አስተያየት መስጫ መድረኮችን በማዘጋጀት አበልጽገው ለምክር ቤቱ የውሣኔ ሃሳብና አስተያየት የማቅረብ፣

2. ቋሚ ኮሚቴዎች የመመርመርና የመከታተል ሥራቸውን የሚያከናውኑት፡-

ሀ. ከሚመለከታቸው መስሪያ ቤቶች አመታዊ እቅድና ክንውን መግለጫ በመቀበል፣

ለ. ስብሰባዎችንና ኮንፈረንሶችን በመሳተፍ፣

ሐ. የሚመለከታቸውን አካላት በመጥራትና በማነጋገር አስፈላጊ ከሆነም መግለጫ እንዲሰጡ በማድረግ፣

መ. ለሥራው መዳበር አጋዥ የሆኑ የተለያዩ የመስክ ጉብኝቶችን በማድረግ፣

ሠ. ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚደርሷቸውን ጥቆማዎችና አቤቱታዎች መነሻ በማድረግ፣

3. ከሌሎች ቋሚ ኮሚቴዎች ወይም አካሎች ጋር ቅንጅት በመፍጠር፣

4. ሪፖርት በማዘጋጀትና ልዩ ልዩ መግለጫዎችን በመስጠት፣

5. በአመታዊ እቅዶች በመመራትና ጠቅላላ አሠራሮችን በመገምገም ይሆናል።

18. የቋሚ ኮሚቴዎች የስብሰባ ሥነ ሥርዓት

1. ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የቋሚ ኮሚቴ አባላት በስብሰባው ከተገኙ ምልዐተ ጉባኤ ይሆናል።

2. የቋሚ ኮሚቴው ውሳኔዎች በአብላጫ ድምፅ ያልፋሉ፣ ሆኖም ድምፁ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሣብ የኮሚቴው ውሣኔ ይሆናል።

3. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው እያንዳንዱ ቋሚ ኮሚቴ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓቱን በተመለከተ ዝርዝር መመሪያ አዘጋጅቶ ለአፈ-ጉባዔው በማቅረብ ያስፀድቃል።

a. Putting up notices;

b. Inviting bodies that give explanations;

c. Preparing forums for public opinion, enriching same and submitting proposals and suggestions to the Council.

2. The Standing Committees shall undertake their investigator and follow up activities by:

a. Acquiring accounts of annual plans and activities from the concern offices;

b. Participating in meetings and conferences;

c. Summoning and consulting concerned bodies for and causing them to give statements, when necessary;

d. Making field visits to strength the task;

e. Embarking upon informations and appeals from various sections of the society;

3. Functioning together with other Standing Committees and bodies;

4. Preparing report and making various statement by preparing reports; and

5. Evaluating general operations on the basis of annual work plans.

18. Meeting procedure of Standing Committees

1. The presence in a meeting of more than half of Standing Committee members shall constitute a quorum.

2. The decisions of a Standing Committee shall be adopted by a major vote; where the vote draws in a tie, the motion supported by the chairperson shall be adopted as the decision of Committee.

3. Without prejudice to the provisions of this article, each Standing Committee shall prepare detailed directives about meting procedure and submit it to the Speaker for approval.

19. የኢኮኖሚ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ

1. የኢኮኖሚ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በዚህ አዋጅ መሠረት ከዚህ በታች የተመለከቱትን መንግሥታዊያን መስሪያ ቤቶች አሠራር ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡-

   ሀ. የገጠር ልማት ቢሮ

   ለ. የንግድ ፣ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ

   ሐ . የውሃና ማዕድን ሐብት ልማት ቢሮ

   መ. ከዚህ በላይ በፊደል ተራ ቁጥሮች ሀ ና ለ ስር ለተጠቀሱ ቢሮዎች ተጠሪ የሆኑ መስሪያ ቤቶችና ድርጅቶች::

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር በተመለከቱት አካላት ስልጣንና ተግባራት ዙሪያ ረቂቅ ህጐችን አዘጋጅቶ ያቀርባል፣ ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ይመረምራል፣

3. የኢኮኖሚ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ና 2 ሥር የተሠጡትን ኃላፊነቶች በተሳለጠ አኳኋን ለመወጣት ራሱን በሚከተሉት ሁለት ንዑሳን ኮሚቴዎች ከፋፍሎ ሥራውን ያከናውናል፡-

   ሀ. የገጠር ልማት ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ፣

   ለ. የንግድ፣ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ::

4. የገጠር ልማት ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ -1- በፊደል ተራ ቁጥር ሀ ስር የተመለከተውን ቢሮና ለእርሱ የሚጠሩትን መንግስታዊያን መስሪያ ቤቶች አሠራር የሚከታተልና የሚመረምር ሲሆን የንግድ፣ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ ደግሞ በፊደል ተራ ቁጥር ለ ስር የተመለከተውን ቢሮና ለእርሱ የሚጠሩትን መንግስታዊያን መስሪያ ቤቶች እንዲሁም በፊደል ተራ ቁጥር ሐ የተመለከተውን ቢሮ አሰራር የመከታተል ሀላፊነት ይኖርበታል፣

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ና 4 የተደነገገው ቢኖርም የሚመለከታቸውን መስሪያ ቤቶች አስመልክቶ የሚዘጋጅ የህግ ረቂቅ ቢኖር ለአፈ ጉባዔው የሚቀርበው በንዑሳን ኮሚቴዎቹ ሳይሆን በኢኮኖሚ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አማካኝነት ይሆናል::

19. Economic Affairs Standing Committee

1. Pursuant to this proclamation, the Economic Affairs Standing Committee shall follow up and monitor the performance of Governmental Offices listed below:

   a. Rural Development Bureau;

   b. Trade, Industry and Urban Development Bureau;

   c. Water and Mineral Resources Development Bureau;

   d. Offices and organizations that are accountable to the bureaux cited under numbers (a) and (b).

2. It shall prepare and submit draft Legislations concerning the power and duties of bodies mentioned in sub-article 1 of this article; monitor, follow up and, when deemed necessary, examine same.

3. The Economic Affairs Standing Committee, with a view to more effectively discharge its responsibilities specified under sub-articles (1) and (2) above, shall undertake its activities by organizing itself into the following two Sub-committees:

   a. Rural Development Affairs Sub-committee;

   b. Trade, Industry and Urban Development Affairs Sub-committee.

4. The Rural Development Affairs Sub-committee shall follow up and examine the performance of the bureau cited under sub-article 1(a) of this Article and the various governmental offices that are accountable offices to it; the Trade, industry and Urban Development Sub-committee shall have the responsibility to follow up the performance of the bureau cited under sub-article (1) (b) of this Article, and all governmental Offices that are accountable to it, as well as the bureau cited under sub-article (1) (c) of same Article.

5. Notwithstanding the provisions of sub-articles (3) and (4) of this Article, any draft legislation prepared concerning the relevant offices shall be submitted to the Speaker not through the Sub-committees, but through the Economic Affairs Standing Committee.

20. የአቅም ግንባታና ማህበራዊ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ

1. የአቅም ግንባታና ማህበራዊ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በዚህ አዋጅ መሠረት ከዚህ በታች የተመለከቱትን መንግሥታዊያን መስሪያ ቤቶች አሠራር ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፦

   ሀ. የአቅም ግንባታ ቢሮ

   ለ. የህዝብ ተሳትፎና አደረጃጀት ጉዳዮች ቢሮ

   ሐ. የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ

   መ. የወጣቶች ባህልና ስፖርት ጉዳይ ቢሮ

   ሠ. የጤና ጥበቃ ቢሮ

   ረ. የማስታወቂያ ቢሮ

   ሰ. ከዚህ በላይ በፊደል ተራ ቁጥሮች ሀ ና ረ ለተጠቀሱት ቢሮዎች ተጠሪ የሆኑ መንግስታዊያን መስሪያ ቤቶችና ድርጅቶች::

2. ከላይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተዘረዘሩትን አካላት በተመለከተ በማናቸውም ሕጐች ተለይተው በተሰጧቸው ሥልጣንና ተግባራት ዙሪያ ረቂቅ ሕጐችን አዘጋጅቶ ያቀርባል፣ ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ይመረምራል::

21. የበጀትና የመንግስት ሂሣብ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ

1. የበጀትና የመንግስት ሂሣብ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በዚህ አዋጅ መሠረት ከዚህ በታች የተመለከቱትን መንግሥታዊያን መስሪያ ቤቶች አሠራር ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

   ሀ. የዋና አዲተር መስሪያ ቤት

   ለ. የገንዘብና ኢኮኖማ ልማት ቢሮ

2. ከላይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተዘረዘሩትን አካላት በተመለከተ በማናቸውም ሕጐች ተለይተው በተሰጧቸው ሥልጣንና ተግባራት ዙሪያ ረቂቅ ሕጐችን አዘጋጅቶ ያቀርባል፣ ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ይመረምራል::

20. Capacity building and Social Affairs Standing Committee

1. Pursuant to this Proclamation, the Capacity Building and Social Affairs Standing Committee shall follow up and monitor the performance of Governmental Offices listed below:

   a. Capacity Building Bureau;

   b. Mass Participation and Organizational affairs Bureau;

   c. Labour and Social Affairs Bureau;

   d. Youth, Culture and Sport Affairs Bureau.

   e. Health Bureau;

   f. Information Bureau;

   g. All Governmental offices and organizations that are accountable to the bureau listed under (a) and (f) above.

2. It shall prepare and submit draft legislations concerning the powers and duties of bodies enumerated under sub-article 1 of this Article, supervise monitor and, examine same.

21. Budgetary and Government Finance Affairs' Standing Committee

1. Pursuant to this Proclamation, the Budgetary and Government finance Affairs' Standing Committee shall follow up and monitor the performance of governmental offices listed below:

   a. Office of the Auditor General;

   b. Finance and Economic Development Bureau

2. It shall prepare and submit draft legislation concerning the powers and duties given specifically to the bodies listed under sub-article 1 of this Article, supervise, monitor and examine same.

22. የህግና አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ

1. የህግና አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በዚህ አዋጅ መሠረት ከዚህ በታች የተመለከቱትን መንግሥታዊያን መስሪያ ቤቶች አሠራር ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡-

   ሀ. ጠቅላይ ፍርድ ቤት

   ለ. ፍትህ ቢሮ

   ሐ. የአስተዳደርና ፀጥታ ጉዳዮች ቢሮ

   መ. ከዚህ በላይ በፊደል ተራ ቁጥር ሐ ሥር ለተመለከተው ቢሮ ተጠሪ የሆኑ መንግስታዊያን መስሪያ ቤቶች::

2. ከላይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተዘረዘሩትን አካላት በተመለከተ በሚኖቸውም ሕጐች ተለይተው በተሰጣቸው ሥልጣንና ተግባራት ዙሪያ ረቂቅ ሕጐችን አዘጋጅቶ ያቀርባል፣ ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ይመረምራል፤

3. ከላይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ቁጥር ሀ ሥር የተጠቀሰውን አካል በተመለከተ ኮሚቴው የነፃ ዳኝነት መርህን በማይጋፋ መልክ የክትትልና የቁጥጥር ሥራውን ያከናውናል፤

4. ምክር ቤቱ ወይም አፈጉባዔው ወደ ማናቸውም ቋሚ ኮሚቴዎች በየጊዜው የሚመራቸውን ረቂቅ ሕጐች ይዘት በተመለከተ ይመረምራል፣ አስተያየት ይሰጣል፤

5. በህገ መንግሥቱ አንቀጽ 48 ንዑስ አንቀጽ 5 የተመለከተውን የህግ ከለላ የማንሳት ጥያቄ ሲቀርብ ለምክር ቤቱ የውሣኔ ሃሳብ ያቀርባል::

23. የሴቶች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ

1. በአዋጅ ቁጥር 60/1994 ዓ.ም አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 5 ስር ለህዝብ ተሳትፎና አደረጃጀት ጉዳዮች ቢሮ የተሠጠው ስለጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የሴቶች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ በዚህ አዋጅ መሠረት የሴቶች ጉዳይ ጽህፈት ቤትን አሠራር ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የሠፈረው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ መንግሥታዊያን አካላትና ድርጅቶች ለሴቶች ሁለንተናዊ ጥያቄ ተገቢውን ትኩረት ሰጥተውና የፆታን ጉዳይ አካትተው የተንቀሳቀሱና የሚንቀሳቀሱ ስለመሆኑ ይከታተላል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ይመረምራል፣ አርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል::

22. Legal and Administrative Affairs Standing Committee

1. Pursuant to this Proclamation, the Legal and Administrative Affairs Standing Committee shall follow up and monitor the work of Governmental Offices listed below:

   a. Supreme Court

   b. Justice Bureau

   c. Administrative and Security Affairs' Bureau

   d. Governmental offices that are accountable to the Bureau cited under number (1)(c) above.

2. It shall prepare and submit draft legislations concerning the powers and duties given specially to the bodies listed under sub-article 1 of this Article; supervise, monitor and examine same.

3. Concerning the body indicated under sub-article (1) (a) of this Article, the committee shall carry out its follow up and monitoring activities without prejudice to the principle of judicial independence.

4. It shall examine the content and essence of draft legislations occasionally referred by the Council or the Speaker to any Standing Committee; and give its own comments and suggestions.

5. Where a demand is submitted for lifting the legal immunity provided for in article 48(5) of the Constitution, it shall make suggestions to the Council.

23. Women Affairs Standing Committee

1. Without prejudice to the powers given to the Mass participation and Organizational affairs Bureau, under the Provisions of Article 13 sub-article5 of Proclamation No. 60/2001, under this Proclamation, the Women Affairs Standing Committee shall follow up and monitor the performance of Women Affairs Offices.

2. Without prejudice to the provisions of sub-article 1 of this Article, the Women Affairs Standing Committee shall follow up and monitor governmental bodies and organizations that give appropriate attention to women's issues and incorporate gender issues in their work agenda; where deemed necessary, it shall examine same and take appropriate actions.

24. በቋሚ ኮሚቴዎች ሥር ስላልተደለደሉ መንግስታዊ አካላት

በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ 19 እስከ 23 በተቋቋሙት ቋሚ ኮሚቴዎች ሥር ያልተደለደሉ መንግስታዊ አካላትን አሰራር በተመለከተ በየትኛው ቋሚ ኮሚቴ አማካኝነት ምርመራና ክትትል እንደሚደረግባቸው በአፈጉባዔው አየታየ የሚወሰን ይሆናል::

25. የጋራ ኮሚቴዎች አሠራር

1. የጋራ ኮሚቴዎች ከአባሎቻቸው መካከል ሰብሳቢውንና ፀሐፊውን ይመርጣሉ፣

2. ከእያንዳንዱ ቋሚ ኮሚቴ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት አባላት በስብሰባው ከተገኙ የጋራ ኮሚቴው ምልዐተ ጉባዔ ይሆናል::

3. የጋራ ኮሚቴዎች ውሳኔዎቻቸውን በአብላጫ ድምፅ ያሳልፋሉ ሆኖም ድምፁ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው የደገፈው ሐሣብ የጋራ የኮሚቴው ውሣኔ ይሆናል::

4. የጋራ ኮሚቴ አባላት በምክር ቤቱ ወይም በአፈ-ጉባኤው አማካኝነት የተመሩላቸውን ጉዳዩች በሚመለከቱበት ጊዜ ሁሉ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 17 ስር በሰፈሩት የአሠራር ስልቶችና ስነ-ስርዓቶች ይጠቀማሉ ::

ክፍል አራት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

26. ደንብ የማውጣት ሥልጣን

በዚህ አዋጅ ውስጥ የሠፈሩትን ድንጋጌዎች ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን ደንቦች ምክር ቤቱ ሊያወጣ ይችላል::

27. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

አፈጉባዔው ይህንን አዋጅና አዋጁን ተከትለው የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል::

28. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ህጐች

ይህንን አዋጅ የሚቃረን ማናቸውም ህግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም::

24. Governmental Bodies not Assigned to under the Standing Committees.

Concerning the performance of governmental bodies not assigned to under the Standing Committees established pursuant to Article 19 to 23 of this Proclamation, the Speaker shall decide which Standing Committee may exercise monitoring and follow up activities over them.

25. Operation of Joint Committees

1. Joint Committees shall elect a Chairperson and a Secretary from among their members.

2. The Presence in a meeting of more than half of members of each Standing Committee shall constitute a quorum.

3. The Joint Committees shall adopt their decisions by majority vote; where the vote draws in a tie, the notion supported by the Chairperson shall be the decision of the Joint Committee decision.

4. Joint Committee members shall, in the process of their deliberations on cases referred to them by the Council or the Speaker, follow the operational methods and procedures specified under Article 17 of this Proclamation.

Part four
Miscellaneous Provisions

26. Powers to Issue Regulations

The Council may issue regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

27. Powers to Issue Directives

The Speaker may issue directives necessary for the implementation of this Proclamation and the regulations issued thereby following this Proclamation.

28. Inapplicable Laws

Any laws, regulations, directives or practices inconsistent with this Proclamation shall not be applicable on matters provided in this Proclamation.

29. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ ዝክረ- ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

ባህር ዳር
መጋቢት 21 ቀን 1994 ዓ.ም
ዮሴፍ ረታ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ፕሬዚዳንት

29. Effective Date

This Proclamation shall come into force on the date of its publication in the region's Zikre Hig Gazette.

Done at Bahir Dar,
this 30th day of March,2002.
Yosef Retta
President of the Amhara National Region